## የሁለተኛው ዙር ዳግም መከፈት መመሪያ

## Coronavirus2019(COVID-19): ለግል አገልግሎቶች የሚያገለግል መመሪያ

## (የፀጉር ቤቶች እና የፀጉር ሳሎን ፣ የጥፍር ፣ የዋክስ ሳሎን ፣ ስፓ)

የሁለተኛው ዙር ዳግም መከፈት ወቅት ፣ ህዝብ እና የንግድ ተቋማት ለሁሉም (COVID-19) የተጋላጭነትን እድል ለመቀነስ አዳዲስ ባህሪያትን እና ጠንከር ያሉ የደህንነት እርምጃዎችን እንዲወስዱ ይጠየቃሉ ። የግል አገልግሎት መስጫ ተቋማት (ለምሳሌ፡ የፀጉር አስተካካዮች እና የፀጉር ሳሎን ፣ የጥፍር / የዋክስ ሳሎኖች እና ስፓዎች) አገልግሎቶችን በቀጠሮ ብቻ ፣ በጠንካራ የደህንነት እርምጃዎች እና ከአካላዊ ርቀት ጋር ሊፈቅዱ ይችላሉ ።በ ሁለተኛው ዙር አገልግሎትን የሚያቀርቡ ከሆነ፤ በሠራተኞች ፣ በደንበኞች እና በማህበረሰቡ መካከል የ **COVID-19** የስርጭት አደጋን ለመቀነስ የሚከተሉት እርምጃዎች መተግበር አለባቸው ። ለተጨማሪ መረጃ coronavirus.dc.gov/phasetwo ን ይጎብኙ።

እባክዎ ያስተውሉ የ COVID-19 ምልክቶች የሚታዩበት ወይም በቅርብ ጊዜ በ COVID-19 ከተያዘ ሰው ጋር ግኑኙነት ያደረገ ማንኛውም ግለሰብ ፤ ሌሎችንም ለበሽታው የማጋለጥ እድል ስላለው የግል አገልግሎት ተቋሙ ውስጥ ለመስራትም ሆነ ለመጎብኘት መገኘት የለበትም ። የ COVID-19 ምልክቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ: ትኩሳት (በግምት ወይም 100.4 ዲግሪ ፋራናይት) ፣ ብርድ-ብርድ ማለት ፣ ሳል ፣ የትንፋሽ ማጠር ወይም ለመተንፈስ መቸገር ፣ ድካም ፣ የጡንቻ ወይም የሰውነት ህመም ፣ ራስ ምታት ፣ አዲስ የጣዕም ወይም የሽታ ስሜት ማጣት ፣ የጉሮሮ መቁሰል ፣ የአፍንጫ መደፈን ወይም ፈሳሽ፣ ማቅለሽለሽ ወይም ማስመለስ ፣ ተቅማጥ ፣ ወይም ደግሞ ጥሩ ያልሆነ የጤና ስሜት።

### ሰራተኞች እና ደንበኞች በየቀኑ የሚከተሉትን የመከላከያ እርምጃዎችን መለማመድ አለባቸው

- ከታመሙ ወይም በቅርብ ጊዜ COVID-19 ላለበት ሰው ከተጋለጡ ቤት ይቆዩ።
- በሚቻልበት ጊዜ ከሌሎች ሰዎች ቢያንስ የ 6 ጫማ ያህል ርቀትን ይጠብቁ፤ እንዲሁም በስራ ቦታ ውስጥ ለአንድ ስታይሊስት / የፀጉር አስተካካይ / የባለሙያ አገልግሎት ቴክኒሻን በአንድ ጊዜ ከአንድ በላይ ደንበኛ አለመፍቀድ ።
- ሰራተኞች እና ደንበኞች ሁል ጊዜ ከጨርቅ የተሰሩ የፊት መሸፈኛዎችን ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።
- ለሠራተኛው መደበኛ ሥራ የመተንፈሻ ቁሳቁሶች ወይም የፊት ጭምብሎች የሚያስፈልጉት ከሆኑ እነዚያ ቁሳቁሶች አሁንም ሊለበሱ ይገባል ። (ከዚህ ጋር በተያያዘ የጨርቅ የፊት ሽፋኖች ተገቢ ምትክ አይደሉም) ። እንደ ቫልቭ ያሉ የመተንፈሻ ቁሳቁሶች የ COVID-19 ስርጭትን ለመከላከል የሚመከሩ ናቸው ።
- በስልክ ወይም በመስመር ላይ ቀጠሮዎችን በሚያስይዙበት ጊዜ፣ ደንበኞች ወደ ንግዱ ተቋሙ ሲገቡ እና አገልግሎቶችን በሚጠቀሙበት ጊዜ የጨርቅ የፊት መሸፈኛ እንዲለብሱ ይጠይቋቸው።
- በተደጋጋሚ እጅዎን ያጽዱ (በሳሙና እና በውሃ ወይም የአልኮል ይዘት ባለው የእጅ ማፅጃ ሳኒታይዘር) ።
    - የእጅ ንፅህናን ማድረግ አስፈላጊ የሚሆኑባቸው ጊዜዎች የሚከተሉትን ያካትታሉ:

- ምግብ ከመመገብ በፊት፣
- መጸዳጃ ቤት ከተጠቀሙ በኋላ፣
- የጨርቅ የፊት መሸፈኛዎችን ከመልበስዎ፣ ከመንካትዎ ወይም ከማዉለቅዎ በፊት እና በኋላ፣
- ከስራ ፈረቃ እና የስራ ዕረፍት በፊት እና በኋላ፣
- ለእያንዳንዱ እንግዳ አገልግሎት ከመስጠት በፊት እና በኋላ ፣
- የእንግዳውን ንብረቶች ከያዙ በኋላ፣ እና
- አፍንጫዎን ካፀዱ፣ ካሳሉ ወይም ካስነጠሱ በኋላ።

## ለአሰሪዎች የሚሰጥ አትኩሮት

- በእያንዳንዱ የስራ ቦታ እና በደንበኞች አካባቢ (ለምሳሌ: የመንበኛ ስፍራዎች እና የመጠባበቂያ ቦታዎች) ተዘውትሮ የእጅ ንጽህና እንዲተገበር (ለምሳሌ: ሳሙና እና ውኃ ወይም 60% የአልኮል ይዘት ያለውን የእጅ ማፅጃ ሳኒታይዘር)አቅርቦቶችን ያዘጋጁ ፡፡
- ለሠራተኞች ተገቢ የግል መከላከያ መሳሪያዎችን (ለምሳሌ፡ ጭምብሎች፣ ጓንቶች) እና የጨርቅ የፊት መሸፈኛዎች ያቅርቡ።
- ጓንት በተለመደው የሥራ ኃላፊነት በተጠቀሰው መሠረት መደረግ እንዲሁም በየደንበኛዉ መካከል መቀየር አለበት፡፡
- ሰራተኞች ንጹህ የሆኑ የስራ ልብሶችን መጠቀም እና ለእያንዳንዱ ደንበኛ ንፁህ ጨርቆችን (እንደ ፎጣ) መስጠት አለባቸው ፡፡
- ከደንበኞች ጋር ቅርብ የሆነ እና ረዘም ላለ ጊዜ የሚደረጉ ግኑኝነቶችን ለሚፈልጉ እንቅስቃሴዎች የፊት መከላከያ ወይም የመከላከያ መነጽር ማቅረብ (<6 ጫማ ከ 15 ደቂቃዎች በላይ)።
- ተለዋዋጭ እና ቅጣትን የማያሳዩ የመልቀቂያ ፖሊሲዎችን ይተግብሩ ፣ እንዲሁም የታመሙ ሰራተኞች ቤት እንዲቆዩ ይፍቀዱ ፡፡
  - የትምህርት ቤት ወይም የሕፃናት መንከባከቢያ ስፍራዎች መዘጋት ያሉባቸው እነደሆነ፣ ወይም የታመሙ የቤተሰብ አባሎቻቸውን የሚንከባከቡ ከሆነ ከልጆቻቸው ጋር አብረው መቆየት ለሚፈልጉ ሰራተኞች ደግሞ የፈቃድ ፖሊሲዎች ተግባራዊ መሆን አለባቸው፡፡

- በተቻለ መጠን ፈረቃዎችን ፣ የመጀመሪያ ሰዓቶችን እና የእረፍት ጊዜዎችን መመደብ፡፡
- ስለ COVID-19 ተቀጣሪዎቹን ማስተማር፡፡ ለተጨማሪ መረጃ ይህንን coronavirus.dc.gov ይጎብኙ፡፡
- ስለ ጥፍር ሳሎኖች የተለየ ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የበሽታ መቆጣጠሪያ እና መከላከያ ማዕከላት (CDC) ን ድረ ገጽ ይመልከቱ: cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/organizations/nail-salon-employers.html፡፡

## መቀራረብን ያስወግዱ እና የመነካካት አጋጣሚዎችን ይቀንሱ

- በእንግዶች እና በሠራተኞች መካከል ቢያንስ የ 6 ጫማ ያህል ርቀትን ለማረጋገጥ የሥራ ቦታዎችን ፣ የጋራ ቦታዎችን ፣ የማረፊያ ክፍሎችን እና ሌሎች የተቋሙ ቦታዎችን ያዘጋጁ፡፡ ማህበራዊ ርቀት አማራጭ በማይሆንባቸው ስፍራዎች የሚያሳዩ መለያያዎችን ወይም ሌሎች አካላዊ መሰናክሎችን ማድረግ ሊያስፈልግ ይችላል ፡፡

- በመጠባበቂያ ቦታዎች ወይም በመውጫ ቦታዎች ውስጥ መሰብሰብን ለመከላከል የእይታ ምልክቶችን ይጠቀሙ። ሰዎች ተቀራርበው እንዳይቀመጡ ወይም ተሰባስበው እንዳይጠብቁ ለማድረግ ከመጠባበቂያ ስፍራዎቹ ወንበሮችን ያስወግዱ ፡፡
- የችርቻሮ ሽቀጣ ሽቀጦችን መንካትወደማየቻልበት ቦታዎች (ማለትም ከባንኮኒ በስተጀርባ) ይውሰዱ።
- በተቻለ መጠን በዲጂታል ስርአቶች በኩል ክፍያውን ይፈጽሙ።
- ከንግዱ አገልግሎት መስጫ ስፍራዎች ለማፅዳት እና ከጀርም ለማስወገዱ የማይቻሉ ከፍተኛ የንክኪ እቃዎችን (ለምሳሌ፡ መጽሔቶች፣ ጋዜጦች) ያስወግዱ።

## ስለበሽታው ምልክቶች ማጣራት እና መከታተል

- በየቀኑ ሰራተኞቹ ወደ የንግድ ተቋሙ ከመግባታቸው በፊት በስልክ ወይም በአካል በመገኘት የሚደረግ ምርመራ (ለምሳሌ: የ COVID-19 ምልክት እንዳለባቸው መጠይቅ) መከናወን አለበት ፡፡
- ከቀጠሮዋቸው በፊት ፣ ወደ የንግድ ተቋሙ ከመግባታቸውም በፊት ፣ በስልክ ወይም በአካል ለደንበኞች ምርመራ ያድርጉ ፡፡፡
- የምርመራ ሂደቶችን ለሠራተኞች እና ለደንበኞች ለማሳወቅ በንግድ ቤቱ መግቢያ ላይ በግልጽ የሚታይ ምልክት ያስቀምጡ ፡፡
- ቢያንስ ለ 30 ቀናት ያህል የተቋሙን አገልግሎቶች ለሚጠቀሙ ግለሰቦች ዕለታዊ መረጃ መዝግበው ይያዙ ፡፡

## ማጽዳት እና ከጀርም ነፃ ማድረግ

- የንግድ ተቋሙ ከፍተኛ የትራፊክ ፍሰት እና ከፍተኛ ንክኪ የሚደረግባቸውን ቦታዎች (ለምሳሌ: ካዉንተር ፣ የክፍያ መገልገያዎችን ፣ መጸዳጃ ቤቶችን ፣ ወዘተ) ቀኑን ሙሉ እና በየደንበኞቹ መካከል በተደጋጋሚ ለማጽዳት እና ከጀርም ነፃ ለማድረግ አጠቃላይ ዕቅድ ሊኖረው ይገባል ፡፡
- መርሐግብሩ በየደንበኞቹ መካከል ለማፅዳት እና ከጀርም ነፃ ለማድረግ በቂ ጊዜ እንዲኖር የሚያስችል መሆን አለበት ፡፡
- የአምራቾቹን መመሪያ በመከተል ሁሉንም የሠራተኛ ጋዎኖች እና የደንበኛ ፎጣዎችን በሚገባ ማጠብ።
- የንግድ ቦታዎችን ስለ ማጽዳት እና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ ስለማድረግ እንዲሁም COVID-19 ን የሚያስከትለውን ቫይረስ ለማጥፋት ውጤታማ ስለሆኑ ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ የማድረጊያ ምርቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የ CDC ድረ ገጽን ይመልከቱ: cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/reopen-guidance.html፡፡

## የግንባታ አትኩሮቶች

- ሕንፃው ረዘም ላለ ጊዜ ከተዘጋ፣ የ HVAC ስርዓቶችን ማየትዎን አይርሱ እንዲሁም ሁሉም የውኃ ስርዓቶች ጥቅም ላይ ለመዋል ደህንነታቸውን የጠበቁ መሆናቸውን ያረጋግጡ። ለተጨማሪ መረጃ፣ ለረጅም ጊዜ ከተዘጉ ወይም ከአጭር ጊዜ የአሰራር ሁኔታ በኃላ ዳግም ለአገልግሎት ስለሚከፈቱ ህንጻዎች የ CDC መመሪያን ይመልከቱ: cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/php/building-water-system.html፡፡

## ለ COVID-19 የመጋለጥ አደጋ ወቅት የሚረዱ እቅዶችን ማዘጋጀት

- አንድ ሰራተኛ ወይም ደንበኛ በ COVID-19 በሚያዝበት አጋጣሚ ወቅት ሊደረጉ ስለሚገባቸው ነገሮች እቅድ ያውጡ፡፡
- በተቋሙ ውስጥ ያለ አንድ ሰራተኛ የ COVID-19 የምርመራ ውጤቱ ፖዘቲቭ ከሆነ እና ይህን መረጃ ማሳወቅ ከፈለገ ሊያሳውቅ የሚችልበትን የመገናኛ ስፍራን ለይቶ ማዘጋጀት፡፡
- አንድ ግለሰብ በስራ ላይ እያለ ከላይ ከተጠቀሱት ምልክቶች የትኛውንም የታየበት ከሆነ ፣ ያ ግለሰብ ወዲያውኑ ራሱን የሚያገልበት ፣ ለተቆጣጣሪው የሚያሳውቅበት እና ተቋሙን ለቅቆ መውጣት የሚችልበት አሰራር መመቻቸት አለበት ፡፡
- አንድ ሰራተኛ የ COVID-19 የምርመራ ውጤቱ ፖዘቲቭ እንደሆነ ለተቋሙ ለማሳወቅ ከወሰነ፣ ተቋሙ ሰራተኞቹ እነዲያውቁ የሚረዳ ለየሚከተሉት የማሳወቂያ ሂደት ሊኖረው ይገባል:
    - የ COVID-19 ፍንጮችን እና ምልክቶችን ጨምሮ ስለ COVID-19 ትምህርት ይሰጣል
    - ለ COVID-19 የምርመራ ውጤት ፖዘቲቭ ለሆኑ ግለሰቦች የግኑኝነት መረጃ መመሪያ ማየት ከፈለጉ በ coronavirus.dc.gov/healthguidance ላይ ማግኘት የቻላል ፡፡
    - በኮሎምቢያ ዲስትሪክት ውስጥ ለ COVID-19 ምርመራ አማራጮች መረጃ በ coronavirus.dc.gov/testingይገኛል።
- አንድ ሰራተኛ የ COVID-19 የምርመራ ውጤቱ ፖዘቲቭ እንደሆነ ለተቋሙ ካሳወቀ፣ **እና** ሰራተኛው ከደንበኞች/ጎብኝዎች ጋር የቅርብ ግንኙነት አድርጎ ከነበር ***ወይም*** ደንበኞች/ጎብኝዎች የ COVID-19 የምርመራ ውጤታቸው ፖዘቲቭ እንደሆነ ለተቋሙ ካሳወቁ፣ ተቋሙ ከሚከተለው መረጃ ጋር በ coronavirus@dc.gov ላይ በኢሜይል ለዲሲ ሄልዝ ማሳወቅ አለበት:
    - በኢሜይል የርዕሰ ጉዳዩ መስመር ላይ "COVID-19 ኮንሳልት"
    - ዲሲ ሄልዝ ጥሪውን ለመመለስ እንዲያስችለዉ በተቋሙ ዉስጥ አመቺ የሆነ የማግኛ ቦታን ስም እና የቀጥታ ስልክ ቁጥር
    - ተጋልጠዋል ተብለው የሚታሰቡ የደንበኞች / የጎብኝዎችን ግምታዊ ቁጥር
    - ስለ ክስተቱ / ሁኔታው የሚገልጽ አጭር ማጠቃለያ።
- የዲሲ ሄልዝ የምርመራ ባለሙያ በ 24 ሰዓታት ውስጥ በተገቢው መንገድ የቀረቡትን የኢሜል ማስታወቂያዎችን የሚከታተል ይሆናል፡፡

ከዚህ በላይ ያሉት መመሪያዎች ወረርሽኙ እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር እየተሻሻሉ የሚቀጥሉ ይሆናሉ፡፡ እባክዎን ለወቅታዊ መረጃ coronavirus.dc.govን በመደበኛነት ይጎብኙ።